# በቁሜ ልናዘዝ

ከኔዓለም

ግዜ መስታወት ነው ሁሉን አየነው
ከሆዱ ተፋቅሮ ህሊናው ከዳው
አገሩን፣ወገኑን፣ሰንደቀአላማውን፣ዜግነቱን ጠላው
ሆድ !ሆድ!ሆድ! ብቻ ነው ምኞትና ዓላማው።

ይህ ሆድ የሚሉት ሁሌየ የማይሞላ
ያስጎበዲድ ያዘ ከፊትና ኃላ
ሆዳም ነህ ተብሎ ህሊናውም በክቶ
ከራሱ ተጣልቶ የሰው ፊትን ሸሽቶ
የበከተው ገላ በሱፍ ተወጥሮ አደባባይ ቆመ እሱ ማንን ፈርቶ።

ይህን የሆድ ነገር እንዳው ስገምተው
ሳይበላ ይቅር የሰው ሥጋ-ደም ነው!
ከዚች የድሃ አገር ከምስኪን ወገኔ
ለምን እለያለሁ በቀረብኝ እኔ
ትውልድ ይቀጥላል ልጄም አፈረብኝ በሆዳሙ በኔ
ለዚህ ለሚያልፍ ቀን ምነው መመዘኔ።

ከህሌና ዳኛ፣ከሐገር፣ከወገን መሸሼ ለምነው
እውነትን ተናግሮ ጾም ማደር ክብር ነው።
ህሊናም አትተው ሁሌ መምገቷ
አንተ ሆዳም ብላ ከኔ መጣላቷ፣

በቁሜ ልናዘዝ ሳለሁ በሕይወቴ

ውሻ ካደረገኝ የገዛ ቀፈቴ

ታንቄ በሞትኩኝ ሳልነግር ላባቴ

ፍትኃትም የለ ሞት ነው መድኃኒቴ።

፩፩/፪፯/፩፩